מדינת ישראל
משרד החינוך
המזכירות הפדגוגית
אגף המפמ#רים
הפיקוח על הוראת אמהרית

## **מיקוד של בחינת בגרות באמהרית (תשע"ח)**

# **የ2018 ዓ.ም. የአማርኛ ባግሩት ፈተና መዋቅር**

የ2018 ዓ.ም. የአማርኛ ፈተና የሚካሄደው ሰኞ ሜይ 28 ቀን 2018 (28/5/2018) ዓ.ም. ነው። የዚህ ዓመት የአማርኛ ፈተና ከታች የተዘረዘሩትን ክፍሎች ይይዛል።

**(ሀ) ባለ 60% (የድሮ 3 ዩኒት) የአማርኛ ፈተና (572381) - የፈተናው አጠቃላይ ነጥብ 60%**

- **ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፡ 2 ሰዓት ተኩል**
- **የፈተናው** *መመሪያዎች* *በአማርኛና በዕብራይስጥ* **ይቀርባሉ። ፈተናው 4 ክፍሎች አሉት።**

### **ክፍል አንድ (የፈተናውን 30% ይይዛል)**

- ይህ ክፍል የሚይዘው *የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለከፍተኛ ተማሪዎች* ከሚለው መጽሐፍ ውስጥ ከገጽ 42 - 55 ከሚገኙ ምንባቦች ውስጥ አንዱን ነው። ከምንባቡ ውስጥ 8 “ደረቅ” ጥያቄዎችና 2 “አመራማሪ” ጥያቄዎች (שאלות עמ"ר) ይቀርባሉ። ተፈታኙ በዚህ ክፍል ለቀረቡት ደረቅ ጥያቄዎች መልሶቹን የሚጽፈው *በአማርኛ ብቻ* ሲሆን ሁለቱ አመራማሪ ጥያቄዎች ከከበዱት በዕብራይስጥም መመለስ ይችላል።[1]

### **ክፍል ሁለት የሥርዓተ ቋንቋ ጥያቄዎች (የፈተናውን 20% ይይዛል)**

- ይህ ክፍል የሚይዘው *የተፈታኙን የመረዳት ችሎታ የሚመዝኑ የሰዋስው እና የሥርዓተ ቋንቋ የምርጫ ጥያቄዎችን* ነው።

### **ክፍል ሦስት (የፈተናውን 30% ይይዛል)**

- ይህ ክፍል የሚይዘው ተማሪዎች ከአሁን በፊት ያልተማሩትን ምንባብ ነው። ከምንባቡም ውስጥ *ደረቅ ጥያቄዎች* እንደዚሁም *የእውነት-ሐሰት ጥያቄዎች* ይቀርባሉ። ተፈታኙ መልሶቹን መስጠት ያለበት *በአማርኛ ብቻ* ነው።

### **ክፍል አራት (የፈተናውን 20% ይይዛል)**

- ይህ ክፍል የሚይዘው ተማሪዎች ከአሁን በፊት ያልተማሩትን ምንባብ ነው። ከምንባቡም ውስጥ *ደረቅ ጥያቄዎች* ይቀርባሉ። ተፈታኙ መልሶቹን መስጠት ያለበት *በአማርኛ ብቻ* ነው።

---

[1] *በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በተባእታይ ጾታ የተጻፉ መመሪያዎች ለአንስታይ ጾታም ጭምር ያገለግላሉ።*

**(ለ) ባለ 40% (የድሮ 2 ዩኒት) የአማርኛ ፈተና (572282) - የፈተናው አጠቃላይ ነጥብ 60%**
አምና በተደረገው "ሒሽታልሙት" እንደተገለጸው የ2 ዩኒት ፈተና ማለትም 40% የሚይዘው የሚዘጋጀው በእያንዳንዱ መምህር ሲሆን የሚከተለው መዋቅር ይኖረዋል። ፈተናው የሚሰጠው ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ነው።

| | **የፈተናው ዓይነት** | **የሚይዘው ነጥብ** |
|---|---|---|
| 1. | ባልታወቀ (unseen) ምንባብ ላይ የተመረኩዙ ጥያቄዎች | 20% |
| 2. | ሰዋስውና የተለያዩ የሥርዓተ ቋንቋ ጥያቄዎች | 25% |
| 3. | ድርሰት (ከ3 እስከ 4 ርእሶች ተሰጥተው ተማሪው አንዱን መርጦ ድርሰት ይጽፍበታል) | 20% |
| 4. | የተወሰነ ርእስ ተሰጥቶ ተማሪዎች የሚጽፉት አጠር ያለ የምርምር ጽሑፍ - | 35% |
| | አጠቃላይ ነጥብ | 100% |

(ሀ) ከ1 እስከ 3 የተጠቀሱትን ነገሮች የያዘውን የጽሑፍ ፈተና መምህሩ አዘጋጅቶ ተማሪዎቹን መፈተን አለበት። በ4 ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ምርምር ግን ጊዜ ስለሚፈጅ መምህሩ ከአሁኑኑ የምርምር ርእስ ሰጥቶ ተማሪው ሥራውን እንዲጀምር ማድረግ አለበት። የምርምር ርእሶች በሒሽታልሙቱ ጊዜ ያከፋፈልኩ ቢሆንም ሊረሱት ስለሚችሉ ወረቀቱን ከዚህ ሚኩድ ጋር አያይዤ ልኬያለሁ።

(ለ) የጽሑፍ ፈተናው የሚዘጋጀው በእያንዳንዱ መምህር ሲሆን ጥራትንና ደረጃን ለማስጠበቅ ሲባል እያንዳንዱ መምህር የሚያዘጋጀውን ፈተና ለእኔ ልኮ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልገዋል። ፈተናውን ለተቆጣጣሪው በሚከተለው መንገድ መላክ ይቻላል።

| ፋክስ ቁጥር፡ | 076-5104175 | ኢ.-ሜይል፡ | teferra@post.tau.ac.il |
|---|---|---|---|

(ሐ) ስለውጤት አሰጣጥ በተለይም የ40% ፈተናን እና የማጌኑን ውጤት ወይም ሌላ ከፈተና ጋር የተያያዘ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ካላችሁ ት/ቤቱ በትምህርት ሚኒስቴር የፈተና ክፍል አስተባባሪ ለሆነችው ለወ/ሮ **ሪቪ ዛኬን** በስልክ ቁጥር 02-5602487 በመደወል ወይም ለኢ.-ሜይል rivkazak@education.gov.il በመላክ መጠየቅ ይችላል።

ከአክብሮት ጋር፡

ዶ/ር አንበሴ ተፈራ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ